***<u>የግል ወገናዊ ጥሪ፤</u>***

***ከ አያል ሰው ደሴ***
***መስከረም ሁለት-ሽህ አራት ዓ/ም*** ***<u>(ክፍል አንድ)</u>***

***ይድረስ፤ ለአገራዊ አንድነት፣ ለፍትኅና ለሕዝባዊ የሥርዓት ለውጥ ለቆሙ ወገኖች ሁሉ!***

***ጉዳዩ:- 'የኢትዮጵያ ብሔራዊ ሸንጎ'ን ስለ-መመሥረትና ለተፈጠረው አደገኛ የሁነኛ <u>ብሔራዊ አማራጭ ክፍተት ምላሽ ስለ-መስጠት፤</u>***

***ክቡራትና ክቡራን ወገን ኢትዮጵያውያን፤***

***የአክብሮት ሰላምታዬን አስቀድማለሁ::***

***ሕይዎታችሁን ሙሉ በአገራችን አዎንታዊ ለውጥ እንዲመጣ የታገላችሁና እየታገላችሁ ያላችሁ የየፖለቲካ ድርጅቶች አባላት፣ የሲቪክና የመያ ማኅበራትና ስብስቦች አባላት፣ አገራችሁንና ሕዝባችሁን ለመታደግ የተጠየቃችሁትንና አቅማችሁ የፈቀደውን ሁሉ ከማድረግ ወደ-ኋላ ያላላችሁ የተከበራችሁ አገር-ወዳድና ዴሞክራት ኢትዮጵያውያን፤***

***ከሁሉ በፊት ይኸ በአራት ተከታታይ ክፍል የሚቀርብ ወገናዊ ጥሪ ረዘም በማለቱ ከፍተኛ ይቅርታ እጠይቃለሁ:: ጉዳዩ ውድ አገራችን ኢትዮጵያንና ለፈተና የተዳረገውንና ለአደጋ የተጋለጠውን ታልቁን ኩሩ ሕዝብ የሚመለከትና ከእያንዳንዳችንም ምላሽ የሚያስፈልገው ተማፅኖ በመሆኑ ወገኖቸ ጊዜ ወስደው መልእክቱን በትዕግሥት እንዲመለከቱት በትኅትናና በታላቅ አክብሮት እጠይቃለሁ::***

***በአስከፊ የስደት ዓለምም ሆነ በአገር ውስጥ በልዩ-ልዩ ዘርፍ በሕወሓት/ኢሕአዴግ አፋኝ አገዛዝ እየተንገላታችሁም እንኳን ድርጅቶች እንደ-ድርጅት፣ የየድርጅቶቹ አባላትም እንደ-አባላት ለአገራችሁና ለሕዝባችሁ ባላችሁ ፍቅር እና ፍትኅንና እኩልነትን የሚያረጋግጥ የተሻለ ሥርዓት በአገራችን እውን እንዲሆን ባላችሁ በጎ ራዕይ ባለ ብዙ ፈርጅ መስዋዕትነት መክፈላችሁና ትግሉን በቁርጠኝነት መቀጠላችሁ የታወቀ ነው:: በአኳያው ይኸ ከምንም በላይ በኅሊና አስገዳጅነት የተያያዛችሁት ትግል የፈለጋችሁት ውጤት እንዳላመጣና የአገዛዙን የጥፋት አጀንዳዎች ማስቆም፣ በአገሪቷና በሕዝቧ ላይ የተቃጡ አደጋዎችን ማስወገድ እንዳልተቻለ፣ የለውጥ-ፈላጊው አካሄድም በአብዛኛው ውሃ-ወቀጣ እንደሆነ የዚያኑ ያኸል ግልጥ ነው:: ያ የሆነው ግን ከእያንዳንዱ ታጋይ በጎ-ፈቃድና ቁርጠኝነት ጉድለት እንዳልሆነም ይታወቃል::***

***ከዚኽም በመነሣት ነው ከጊዜ-ወደ-ጊዜ እየከፋ የመጣው የአገራችን ሁኔታ ጨርሶ መመለስ የማይቻልበት ደረጃ ላይ ሣይደረስና ሕዝባችን ለአጠቃላይ ትርምስ እንዳይዳረግ አፍራሽ ሂደቱን ለመግታት፣ ለሕዝባችን ፍትኅንና እኩልነትን፣ ለውድ አገራችንም አንድነትን ለማረጋገጥ ያለን በጎ ራዕይ ለውጤት እንዲበቃ ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነትን መሠረት ባደረገ አዲስ መንፈስ፣ አዲስ አደረጃጀትና አሠላለፍ መያዝ ይኖርብናል የሚል አሣቤን ለማካፈል የተገደድኩት:: ይኸንን ጥያቄ-አዘል የምር ጥሪ ለኢትዮጵያውያን ወገኖቸ የማቀርበው የተለዬ ችሎታ ኖሮኝ ወይም ሕዝባችን የሚገኝበት እየከፋ የሄደ ሰቆቃ፣ በቁም እየሞተች ያለችው የአገራችን ሁኔታና እያንዣበበ ያለው የጎልውና-ማጣት አደጋ በአንድ በኩል፣ የለውጥ-ፈላጊው ኃይል መጣኝ ምላሽ ለመስጠት ዝግጁነት ማነስና ይበልጡንም ብትን-ያለና አቅጣጫ የሣተ አካሄድና ይዞታ በሌላ በኩል ለሌሎቻችሁ አልታያችሁም፣ አያሣስባችሁምና አይቆረቁራችሁም ከሚል ግብዝ ግምት ሣይሆን፤ እንደ-አንድ አገር-ወዳድ ዴሞክራት ኢትዮጵያዊ እነኝኽ ተደማምረውና ተጋግዘው ለፈጠሩት የሁነኛ ብሔራዊ አማራጭ ያለመኖር አደገኛ ክፍተት የምር አሣሳቢነትና አስቸኳይ ምላም ሊሰጠው እንደሚገባ ያለኝን አሣብ ለማካፈል በመድፈር ነው::***

***እነዚኽ የሚታዩ አደጋዎችም እንኳን ባሉበት በዚኽ ፈታኝ ጊዜ፣ ይዋል ይደር እንጂ ውድ አገራችን ኢትዮጵያ አንድነቷ እንደሚከበር፣ ኩሩው ሕዝቧ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓትን***

እንደሚጎናፀፍ፣ የአምባ-ገነን የአገዛዝ ሥርዓቶች አዙሪት ተሰብሮ፣ ረሃብ፣ ችግርና ኋላ-ቀርነት ታሪክ እንደሚሆኑ የጠና እምነት አለኝ:: ወደዚያ ብሩኅ ተስፋ አስጨባጭ አይቀሬ-ግብ ለመድረስ ግን አሁን ያሉ አደጋዎችን በጊዜ ነቅተንና በድፍረት ተጋፍጠን፣ መድረስ የሌለበትንና ከወዲኹ መወገድ የሚችልን ማንም ተጠቃሚ የማይሆንበት ያላስፈላጊ የጥፋት ድግስ ማስወገድና ክቡር የሆነው የሰው ሕይዎትና ንብረት አጓጉል እንዳይባክን አገራችንና ሕዝባችንን መታደጉ ተገቢም የዜግነት ግዴታም አድርጌ በመውሰድ ነው ወገናዊ የተማፅኖ ጥሪየን ለወገኖቸ የማቀርበው::

በዚኽ ረገድ አንዳንድ ለአዎንታዊ ለውጥ በቆሙና በሚታገሉ የፖለቲካ ድርጅቶችና የሙያና ልዩ-ልዩ ሕዝባዊ ስብስቦች ከመግለጫ ማውጣት ጀምሮ የመሰባሰብ ጥረቶች እየተደረጉ መሆናቸው ይታወቃል::

መቼም ቢሆን ትግሉ ያለን ሁኔታ ለመቀየር የሚደረግ ጥረት በመሆኑ ሁሉም ነገር በራሱ ሂደት ዝም-ብሎ የሚስተካከልበትን ጊዜ ጠብቆ የሚካሄድና ያ ጊዜ እስኪመጣ ግን አንገት ደፍቶ መቀመጥ እንዳልሆነ ይታወቃል:: ስለሆነም ለአዎንታዊ ለውጥ የቆመው ኃይል የሚያደርገውን ትግል ሊወስን የሚገባው ከገኸው ባኅሪ ይበልጥ ሕዝብ ሊቀበለውና ሊታገልለት የሚችል የተሻለ አማራጭ የያዘና ያን የተሻለ አማራጭም ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችል፣ ሕዝብ አመኔታውንም፣ ከበሬታውንም ሊለግሠውና እሱንም ማዕከል ያደረገ ትግል ለማድረግ የሚያበቃ አደረጃጀት መያዝና ብቁ ሆኖ መገኘትና አለ-መገኘት ይሆናል::

ክቡራትና ክቡራን ወገን ኢትዮጵያውያን፤

ጉዳዩን በክፍል በክፍል ለማሣየት ልሞክር::

<u>አንደኛ፡ የምንገኝበት ሁኔታ፤</u>

በእኔ አመለካከት የወቅቱ የአገራችን አጠቃላይ ሁኔታ በአጭር አገላለጥ **በጣም አስከፊና ፈታኝ፣ እጅግ አሣሣቢና በዙሪያ-ጥምጥም ውጥረት የተሞላ እና አደገኛ ክፍተት** የተፈጠረበት ነው ማለት ይቻላል::

ሕዝባችን ታይቶ-ተሰምቶ ለማያውቅና ሊሸከመው ላቃተው አንገፍጋፊ የኑሮ ውድነትና ለነቀዘ ሙስና፣ ዓይን-ላወጣና ይሉኝታ-ቢስ ዘረፋ የተዳረገበት፣ በአገሩ ላይ ተስፋውን እንዲቆርጥና ባይተዋር እንዲሆን በሚያደርገው ከባድ ችግር ውስጥ የወደቀበትና እንደ-ሕዝብ ኅልውናው  አደጋ ላይ ያለበት ጊዜ በመሆኑ **እጅግ አስከፊና ፈታኝ፤**

ሕዝብ ለከት ለሌለው የፖለቲካ እመቃና ወደ-እርስ-በርስ ግጭት ለሚገፉፉ ቅጥ-ያጣ አድሎዓአዊ ጭቆና የተዳረገበት፣ ልዩነትን መሠረቱ ባደረገ የአገዛዝ ሥርዓት ምክንያት በኅብረተሰቡ ልዩ-ልዩ ክፍሎች መኻል አለመተማመንና ጥርጣሬ እንዲሰፍን እየተደረገ፣ ቅጥ-ያጣ የሃብት ክምችት በጣም በጥቂቶች እጅ እየሆነ በአንፃሩ ቁጥሩ እየጨመረ የሄደው ምልዓተ-ሕዝብ ለአጣ-ለነጣ ድህነት እየተዳረገና በሃብታምና በድሃው መኻል ያለው ልዩነት በሚሰቀጥጥ መልክ እየጎላ የመጣበት፣ በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ዜጎች ለአዋራጅ የረሃብ አዙሪት የተዳረጉበት፣ በአገራቸው ተስፋቸውን ያሟጠጡ ሥፍር-ቁጥር የሌላቸው ወገኖቻችን (በተለይ ወጣት ሴቶቻችን) ዘመናዊ ባርነት ሊባል ለሚችል ሰብዓዊ ክብር-ነኪ፣ ዋስትና-የለሽና አሣፋሪ የግርድና ሥምሪት ወደ-አረብ አገሮች እየጎረፉና ሌሎችም ባገኙት አጋጣሚና ባመቻቸው መንገድ ሁሉ ከአገራቸው በመሰደድ ላይ ያሉበት፣ ከመቸውም ጊዜ ይበልጥ ጎሣን/ዞግን መሠረት ያደረገ የልዩነት መስመር በጣም በጎላና በሚታይ መልኩ እየተሠመረና ሕዝባችን ለአስፈሪና አደገኛ ትርምስን-ዳራጊ ውጥረት እየተመቻቸ ያለበት፣ ለሰመመ ተስፋ-መቁረጥና ቀጣይ ስጋት የተጋለጠበት፣ ለሃብቱ ይሁን ለሕይዎቱ፣ ለሥራው ይሁን ለመብቶቹ ምንም ዓይነት አስተማማኝ የዜግነት ዋስትና የጠፋበት፣ “በኤኮኖሚ አውታሮች ግንባታ፣ ልማትና 'ትራንስፎርሜሽን'” ስም ሕዝብ በቁሙ እየተዘረፈ፣ አገሩ ለውጭ ባዕዳን መዋዕለ-ንዋይና ጥሪት-አፍሳሾች (ኢንቬስተርስ) በሃራጅ እየተቸበቸበችና ሕዝባችን በሕወሓት/ኢሕአዴግ ጢሰኝነት ፍዳውን መክፈሉና መከራውን ማየቱ አልበቃ አለና ይባስ ተብሎ ዜጎች ለባዕዳን ጢሰኝነትና ለአዋራጅ የሦስተኛ(*1) ደረጃ ዜግነት

እንዲዳረጉ እየተደረገ ያለበት፣ ሕዝብ አቅም እያለው አቅም-የለሽ ሆኖ እንዲገኝ የተደረገበት፣ ሕዝባችን ባህላዊ እሴቶቹን እንዲያጣ ለሚያደርጉ ርካሽ ልማዶች እንዲሁም ለማንኛውም አክራሪ ዝንባሌዎች እየተጋለጠና በማንኛውም ጊዜ ሊፈነዳ ለሚችል ከፍተኛ ውጥረት የተዳረገበት ሁኔታ ስለሆነ በጣም አሣሣቢና በዙሪያ-ጥምጥም ውጥረት የተሞላ፤

ሕዝባችን ለዚኸ ሁሉ መከራ ተዳርጎና ለፈርጀ-ብዙ አደጋዎች ተጋልጦ ባለበት በዚኸ ፈታኝ ጊዜ፤ በአንድ በኩል ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነትን ጠላት አድርገው የፈረጁና የውጭ ባዕዳን አደፋፋሪነትና ድጋፍ ያልተለያቸው ታጣቂ ተገንጣይ ኃይሎች የሚራወጡበት፣ በአገዛዙ ሕዝብን ከፋፋይ መሠሪ የፖለቲካ ፍልሥፍንናና መርኖ ምክንያት ኢትዮጵያውያን ተለያይተው እንዲያድጉ፣ ማኀበራዊ ትሥሥሮችና በረጅም-ጊዜና በብዙ መስዋዕትነት የተገነባ አገራዊ አንድነት፣ ኢትዮጵያዊ ማንነትና የዜግነት ኩራት የሆኑ ብሔራዊ እሴቶች ሆን-ተብሎ እየተሸረሸሩ የመጡበትና በዚኸም ምክንያት ዜጎች ከአጠቃላዩ የጋራ ጥቅምና ትሥሥር ይበልጥ በይስሙላዊ መብት ስም የቡድነኝነት/ጎሠኝነት ስሜት ላይ እና የየአካባቢው ላይ እንዲያተኩሩ የተደረገበት፣ አክራሪ አዝማሚያዎች ሰርገው ለመግባት አመቺ ሁኔታ የተፈጠረበት፣ በሌላ በኩል ሁሉንም እንደፈለጉና እንዳሻቸው ማድረግ አንጡራ መብታቸው እንደሆነ የሚቆጥሩትና የ"እኔ ከሞትኩ ሰርዶ አይብቀል" እምነት የተጠናወታቸው እራስ-ወዳድና ግብዝ የሕወሓት/ኢሕአዴግ መሪዎች ሁኔታው ለነሱ ካላመቻቸው የአገሪቱንና የሕዝቧን አንድነት ጭምር ከጎልውናቸው ጋር እንዲተሣሰር እየደከሙ ያሉበት ሲሆን፤ በአንፃሩ ግን ሕዝቡ አመኔታውን የሚጥልበት፣ የተሻለ ብሩኅ ተስፋ የሚፈነጥቅለት፣ ለሕወሓት/ኢሕአዴግ አፋኝ አገዛዝ ሁነኛና አስተማማኝ አማራጭ የሚሆንና በቁርጠኝነት ታግሎ የሚያታግለው ብሔራዊና አገር-አቀፍ ተለዋጭ ኃይል ባለመኖሩ ደግሞ አደገኛ ክፍተት የተፈጠረበት ሁኔታ ውስጥ ነን ለማለት የቻልኩት።

በእርግጥ የወቅቱን የአገሪቱ ሁኔታ ከዚኸ በተለየ መነፅር የሚያዩ ወገኖች እንዳሉ ግልጥ ነው። መቼም ጤናማ የኤኮኖሚ እድገትን፣ በተለይ እሳፋሪና አዋራጂ ረሃብን ከአገር ለማስወገድና የኢትዮጵያ ሕዝብ በተቻለ ፍጥነት የምግብ ዋስትና እንዲኖረው የሚያስችልና የሚያረጋግጥ ልማት እንዲሁም የመገናኛ አውታሮችና ግድብን የመሣሰሉ ከፍተኛ ብሔራዊ-ጠቀሜታ ያላቸው የልማት ተቋሞች ግንባታን የሚቃዎም ጤናማ ዜጋ የሚኖር አይመስለኝም። አገራችንን በምግብ እራሷን እንድትችል ማድረግና ለሕዝባችን የምግብ ዋስትናን ማረጋገጥ "ከተመቸኝ" ተብሎ የሚደረግ ቅንጦት ሣይሆን መሠረታዊ የሰብዓዊ መብት ጉዳይ ተደርጎ ሊታይ የሚገባው፣ ይኸንን ማሟላት ደግሞ ለማንኛውም መንግሥት ግዴታ በመሆኑ በዚኸ ረገድ የሚደረግ ማናቸውም ቀና ጥረት ሊደገፍ የሚገባው ነው።

ቀደም-ሲል የነበሩ በውስጥ የርስ-በርስ ጦርነትና የውጭ ዕብሪተኛ ተስፋፊዎችን በመከላከል ተጠምደው አገራቸውን 'በጦርነት ኤኮኖሚ' ማንቀሣቀስ የተገደዱ የአፄ ኃይለ-ሥላሴና የኮሎኔል መንግሥቱ መንግሥታት የገጠማቸው ፈተና ያልገጠመውና እነዚያ ሊያገኙ ያልቻሉትን የውጭ እርዳታ በልዩ-ልዩ ሰበብ-አስባብ በገፍ እያገኘ ያለው ሕወሓት/ኢሕአዴግ የአገሪቱን ሃብትና ጥሪት መሪዎቹንና ደጋፊዎቻቸውን ማበልፀጊያና የተረፈውንም ሕዝብን በማፈን አሉታዊ ጥረት ላይ ከማዋልና አሁን በሚሠሩ አንዳንድ እንቅስቃሴዎች ምሥጋናን ለማግኘት በምፀት ከመግደርደር ይልቅ፣ ከሚታየው በእጅጉ በላቀ ሁኔታ ሕዝብ እየመከረባቸውና ዝርዝርና ተኣማኒነት ያላቸው ጥናቶች የተደረገባቸው አገርንና ሕዝብን ተጠቃሚ የሚያደርጉ የልማት ሥራዎች በስፋት እስካሁንም መደረግ ነበረባቸው አሁንም ሊደረጉ ይገባል። አሁን በከተሞች፣ በተለይም በአዲስ-አበባ፣ ፍንጥቅ-ፍንጥቅ ያሉ ባዶ ህንፃዎች በመገተራቸው፣ አንዳንድ የግንባታ ሥራዎች በመታየታቸው፣ ለአገዛዙ ቁንጮች ብቻ የሚታወቁ "የኤኮኖሚ እድገት" አኃዞች እየተዥጎደጎዱ ጧት-ማታ በመለፈፋቸው፣ የውጭ ባለ-ሃብቶች የሚያደርጉትን የተፈጥሮ ሃብት ቅርምትና አንዳንድ እንቅስቃሴዎች በማየት ለሕዝብ የሚተርፍ እድገትና ብልፅግና እንዳለ የሚቆጥሩ ክፍሎች መኖራቸው ግልጥ ነው። አዎን፤ እነሱ ቁንጣን ሲይዛቸው ሌላው ጠግቦ ያደረ የሚመስላቸው፣ በእነሱ ላይ እስካልተተኮሰ ድረስ ዜጎች በጠራራ ፀሐይ በአገዛዙ ታጣቂዎች ሲረሸኑ፣ ሰብዓዊ መብታቸው ሲገፈፍ፣ ሰብዓዊ ክብራቸው ሲረገጥ፣ ከመሬታቸው በግፍ ሲፈናቀሉ፣ በአገራቸው ባዕድ ሆነው እንዲታዩ ሲደረግ፣ ወዘተ ሁሉም ሰላምና በሕግ የሚተዳደር አድርገው የሚቆጥሩ፤ በአጠቃላይ ሁኔታዎችን ሁሉ ሕወሓት/ኢሕአዴግ

*ባጠለቀላቸው የመነፅር ቀለም ብቻ የሚያዩና የገረጣውንና የጨወለገውን ሁሉ አረንጓዴና ለምለም፣ ለሕግ-የበላይነትና ለእኩልነትና ለአንድነት የሚታገሉ ወገኖቻቸውን በ"ሕገ-መንግሥት አፍራሽነት"፣ በ"ፀረ-ልማትና ፀረ-ሰላም"፣ አልፎም በ"አሸባሪነት"፣ ወዘተ. አደገኛ "ጠላቶች" አድርገው የሚያዩ፣ ሁኔታዎችን ሁሉ በተሰጣቸው ሕወሓት/ኢሕአዴግአዊ ጎሠኛ/ጎጠኛ የመነፅር ቀለም ሥር የሚመለከቱ ጥቅም-አደርና አጎብዳጅ ዜጎች እንዳሉም ይታወቃል።*

*በዚኽ ፈታኝ ጊዜ ምክንያቱ ሊለያይ ቢችልም አገዛዙን ተቃውሞ ለለውጥ በሚታገለው ወገን ብቻ ሣይሆን ከሕወሓት/ኢሕአዴግ መሪዎች ጀምሮ አባላትና ደጋፊዎች ጭምር በአገራችን ለውጥ እንዲመጣ የማይፈልግ የለም ማለት ይቻላል። የኢሕአዴግ መሪዎች የሚፈልጉት ለውጥ ግን ያለው ሁኔታ ባለበት መቀጠል አለ-መቻሉን ከመገንዘብና ያ ደግሞ ከንም በላይ የጎልውናቸው ዋስትናና የሞት-የሽረት ጉዳይ አድርገው የሚያዩትን ሥልጣን እስከ-ቻሉ ድረስ የሙጥኝ ለማለት፣ ሙሉ ቁጥጥራቸውን እንዳያጡና ተጠያቂነትንም ከመፍራት አስቀድሞ ይዞታቸውን ለየት ባለ መልክ ሊያስቀጥል የሚያስችል ጥገናዊ መንገድን ከመሻት ነው። ሕዝብና ታጋዩ ለውጥ የሚፈልገው ደግሞ ኢሕአዴግአውያን "ያገኙትን" እንዲያጡ ወይንም ላደረሱት በደል ለመበቀል ሣይሆን እነሱ ለመኖር ሌላው መሞት፣ እነሱ ለመክበር ሕዝብ መደህየት፣ አገዛዙና ሸሪኮቻቸው ተደላድለውና ተንደላቀው ለመኖር ዜጎች መፈናቀል፣ መሰደድና መንገላታት፣ ሰብዓዊ ክብራቸውና መብቶቻቸው መረገጥና መገፈፍ ስለሌለበት፣ አድልዖ፣ ሙስና፣ አገራዊ ውርደትና ኋላ-ቀርነት እንዲወገዱ፣ ፍትኅና እኩልነት ለሁሉም የአገሪቱ ዜጎች (አሁን ለሚጨቁኗቸውም ጭምር) እንዲሰፍኑና አጠቃላዩን የጋራ ጥቅም በማሰብና በማለም ነው። ተራ የኢሕአዴግ አባላትና ደጋፊዎቻቸው ከላይ ሲታይ ሥራቸውንና ጊዚያዊ ጥቅማ-ጥቅማቸውን እንዳያጡ በመስጋት ያለው ሁኔታው የአገዛዙ ቁንጮዎች በፈለጉት መልክ እንዲቀጥል የሚፈልጉ ቢመስልም፣ ኑሯቸውና የወደፊት ዕጣ-ፈንታቸው ከሠፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ የተለየ ባለ-መሆኑ ውስጣዊ ስሜታቸው ከለውጥ ፈላጊው ሕዝብ የተለየ እንደማይሆን፣ አካሄዳቸው ግን የኃይል ሚዛንን የተከተለ እንደሚሆን አያጠራጥርም።*

*ማንኛውም በአገራችን አዎንታዊ ለውጥ ለማምጣት አሳብ ያለውና የሚታገል አገር-ወዳድና ዴሞክራሲያዊ ድርጅትም ሆነ ስብስብ ቀጣይ ሕዝባዊ ትግሉ ለአዎንታዊ ውጤት እንዲበቃ የሚደረገው አዲስ ጥረት ሁሉ አገራችን የምትገኝበትን ይኽን አደገኛ የቀውጢ ሁኔታ በቅጡ ያገናዘበ፣ አነሣሱ፣ አሠላለፉም ሆነ አደረጃጀቱና አካሄዱ ያሉትን አደጋዎች የሚያስወግድና ለዴሞክራሲያዊ (ሕዝባዊ) ሥርዓት ግንባታ ሁኔታዎችን የማመቻቸት ኃላፊነትን በብቃት መወጣት የሚችል ሁነኛ <u>ብሔራዊ አማራጭ</u> ማቋቋምን የቅርብ ጊዜ ዋነኛ ዓላማው ያደረገ ሊሆን ይገባል።*

*የአገራችን ሁኔታ ከዚኽ በላይ በአጭሩ የተገለጠው መሆኑን ካመንን፣ ለውጥ-ፈላጊው አገር-ወዳድና ዴሞክራት ኃይል አሁን የሚገኝበት ይዞታም ሆነ እስካሁን በተጓዘበት የአደረጃጀት ዘይቤና የኃይል አሠላለፍ ሕዝብና አገርን የሚታደግ አዎንታዊ ለውጥ ማስገኘት እንደማይቻል ከተገነዘብን እና ሁለቱ ተዳምረው በአገራችን የፈጠሩትን የሁነኛ ብሔራዊ አማራጭ ያለመኖር የሚያስከትለውን አደጋ ከተረዳን፣ ይኽ ክፍተት መደፈን እንዳለበትና ለውጥ እንደሚያስፈልግ እምነታችን ከሆነ፤ በመሠረታዊ የአስተሣሰብ ለውጥ ላይና በኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት እምነት ላይ የተመሠረተ አዲስ የኃይል አሠላለፍ ሊኖርና ሕዝባዊ ትግሉን በማዕከልነት ሊመራ፣ ለሕዝባችንም ሁነኛ አማራጭ በመሆን የተፈጠረውን አስጊና አደገኛ ክፍተት መድፈን የሚችል የፖለቲካ ድርጅቶች፣ ልዩ-ልዩ ብሔራዊ ተቋማት፣ የሲቪክና ሙያ ማኅበራትና ስብስቦች፣ ምሑራንና የአገር-ሽማግሌዎች የሚወከሉበት፣ በተለዋጭ መንግሥት ደረጃ የሚንቀሣቀስና ታግሎ የሚያታግል <u>"የኢትዮጵያ ብሔራዊ ሸንጎ"</u> ሊመሠረት ይገባል እላለሁ።*

*ይኽ አካል እንዴት እንደሚመሠረት፣ አደረጃጀቱን፣ አወቃቀሩንና አሠራሩን በተመለከተ ያለውን ዝርዝር ባስፈላጊው መድረክ ላይ ለሚመለከታቸው አካላት እንደማቀርብ ከወዲኹ ቃል እየገባሁ፣ የገጠሙንን እክሎችና የጋራ ድክመቶቻችንን፣ መደረግ የሚኖርባቸውን አንዳንድ ጉዳዮችንና ቀጣይ እርምጃዎቻችንን ላቅርብ።*
***በክፍል ሁለት ይቀጥላል....***